## ልቤን ይሰብረዋል

ልቤን ይሰብረዋል ድንግል ኀዘንሽ
ሆዴን ይብሰዋል ድንግል ስደትሽ
እጅግ ያሳዝናል ማርያም መከራሽ
አዝ . . . . .

በዚያ ምድረ በዳ በቃዴስ ሐሩር
ውኃ ጥም ጸንቶብሽ አገር በመዞር
ሲዘባበቱብሽ የግብፅ ሴቶች
መች አገኘሽና ለአንቺ የሚመች

አዝ . . . . .

ድንግል ስትለምኚ ያባረሩሽ ሁሉ
ተሰነጣጠቁ በቁም ተከፈሉ
የክርስቶስ እናት ቀረና መሆንሽ
እንደ አንድ ተራ ሰው ስንቅ ተያዘልሽ

አዝ . . . . .

ያዘልሽውን ንጉሥ ኮቲባ ዘንግታ
ወረወረችው ምድር የፍጥረቱን ጌታ
ዮሴፍ ጠባቂሽ ነው ጌታውን አክባሪ
ደረሰው በሕልው የመልአኩ ጥሪ

አዝ . . . . .

በቃ ስደታችሁ ሞቷል ያ መሠሪ
በማለት ነገረው ገብርኤል አብሣሪ
ተመለስ አገርህ ወደ ናዝሬት ግባ
ደስታ ይብዛላችሁ ከእንግዲህ አታንባ
ብሎ ባዘዘው ቃል እንግልቱ በቃ
የክርስቶስ ስደት የድንግል ሰቆቃ